የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት

☏ +251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251 116– 55 12 56 Fax. +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa, Ethiopia e-mail:-allethiopiaunityparty@gmail.com

ALL ETHIOPIA UNITY PARTY

ቁጥር
Ref No. 15/12/2004
ቀን
Date

# ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት የሚሆንበት ሁሉን አቀፍ ኮንፍረንስ እንዲጠራ መኢአድ ይጠይቃል፡፡

ኢትዮጵያ ለዘመናት የተለያዩ አኩሪ እና አሳዛኝ ታሪኮችን አስተናግዳለች፡፡ አገራችን የአክሱም ሃውልትን፣ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን፣ የፋሲል ግንብን፣ የጀጎል ግንብን እና ሌሎችም በርካታ አኩሪ የሥልጣኔ ዘመናትን አሳልፋለች፡፡ እጅግ ለማመን አስቸጋሪ የሆኑ አገራዊ ድሎችንም በህዝባችን ጥንካሬ አግኝታለች፡፡

ባንፃሩ ሃገራችን በተለያዩ ጊዜያት ያጋጠማት ረሃብ ብዙ ህይወትን ቀጥፏል፡፡ ኢትዮጵያንም በመጥፎ ገጽታ ለዓለም አስተዋውቋታል፡፡ እስከዛሬ ሊወገዱ ያልቻሉ ኋላ ቀርነት፣ መሃይምነት፣ ድህነት፣ ደም አፋሳሽ ግጭት፣ እና ሌሎችም ዛሬም ድረስ ተከትለውን እየቀጠሉ ያሉ ክፉ ገጽታዎች ናቸው፡፡

የኢትጵያ ህዝብ  በቀድሞውና አሁን ባለው በሁለት ተከታታይ አንባገነን መንግሥታት ከፍተኛ የመከራ ህይወትን ገፍቷል፡፡ መገደል፣ መታሠር፣ ከቀዬና ከሥራ መፈናቀል፣ መራብና መጠማት፣ በሥራ ማጣት መንከራተት፣ ከሃገር መሠደድ፣ ሃሳብን በነፃነት ለመግለጽ መታፈን እና ሌሎችም መከራዎች ዕጣ ፋንታዎቹ ሆነዋል፡፡ እንግልትና ሰቆቃ ያንገሸገሸው ህዝብ የፍትህ ያለህ እያለ ሲጮህና ሲያነባ ይኸው አርባ ዓመት ሊሞላው ጥቂት ቀርቶታል፡፡

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ማለቂያ ያጣውን የህዝብ ስቃይ ለማስቆምና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በሃገሪቱ እንዲሠፍን ለማድረግ ለሃያ ዓመታት የታገለ ፓርቲ ነው፡፡ መኢአድ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ ከህዝብ ጋር በመሆን በጽናት በመታገል ላይ ይገኛል፡፡ ፓርቲያችን ህዝብ በወደደውና በመረጠው መሪ የሚተዳደርበት ሥርዓት እንዲመጣ በቁርጠኝነት ይታገላል፡፡ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት አባላትና ደጋፊዎች ላለፉት ሃያ ዓመታት ክቡር ህይወታቸውን በመገበር ጭምር ቁርጠኛ ትግል አካሂደዋል፡፡ መኢአድ በመላው ኢትዮጵያ ባሉ ክልሎች ውስጥ መዋቅሩን ዘርግቶ በስፋት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ ህብረ ብሔራዊ ፓርቲ መሆኑም ይታወቃል፡፡

ዛሬ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በወያኔ ኢሕአዴግ እየደረሰ ያለው አፈናና እረገጣ አስከፊ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ አምባገነናዊ የወያኔ ሥርዓት ህዝቡን ነፃነት በማሳጣት፣ ሰላም በመንሳትና በድህነት አረንቋ ውስጥ በመጣል አስከፊ ህይወት እንዲኖረ እያደረገ ይገኛል፡፡ ሥርዓቱ ዘርፈ ብዙ አገራዊ ችግሮችን አስከትሏል፡፡ ዛሬ አብዛኛው ሰው በሰላም ሰርቶ ለመኖር እያዳገተው ይገኛል፡፡ ወያኔ ኢህአዴግ በሃገራችን ላይ ካስከተለው መጠነ ሰፊ አገራዊ ቀውሶች የቲወሰኑትን በጥቂቱ መመልከት ይቻላል፡፡

1. የወያኔ ኢህአዴግ መንግሥት በክርስትና እና በእስልምና ሃይማኖቶች ውስጥ ጣልቃ በመግባት ምዕመናንን አስሯል፤ ደብድቧል፤ ለሃይማኖታዊ ሥርዓታቸው የሚጠቀሙበትን መሬት ነጥቋል፤ መሪዎቻቸውን በራሳቸው ተቋማት ውስጥ እንዳይመርጡ ከልክሏል። እነዚህንና ሌሎች በደሎችን ፈጽሟል፤ አሁንም በመፈጸም ላይ ይገኛል።

2. ወያኔ ገና ከጅምሩ ህወሃትን ሲጠነስስ ዓላማ አድርጎ በተነሳው የጎሳ ፖለቲካ በወንድማማችነትና በእህትማማችነት ተዋዶና ተከባብሮ፣ ተጋብቶ እና ተዋልዶ የኖረውን ህዝብ ለማለያየት ብዙ ጥረት አድርጓል። የአገራችንን አንድነት የሚያናጉ የተከፋፈለ ማኅበረሰብ ለመፍጠር የተወሰዱት እርምጃዎች በሰው ህይወትና ንብረት ላይ ብዙ ጉዳት አድርሰዋል። በቅርብ እንኳ በደቡብ ኢትዮጵያ በቦረናና በጋሪ ህዝብ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት የሰዎችን ህይወት ከመቅጠፉ በተጨማሪ ብዙዎችን ለስደት ዳርጓል። በአርባጉጉ፣ በገለምሶ፣ በአርሲ፣ በበደኖ፣ በጋምቤላ፣ እና በሌሎችም አካባቢዎች የጎሳ ፖለቲካ የፈጠራቸው ችግሮች ለብዙ ህይወት ማለፍ ምክንያት ሆኗል። በአንዳንዶቹ አካባቢዎችም በመኖሪያ ቤትና በደረሱ ሰብሎች ላይ ቃጠሎ ተፈጽሟል። አሁንም በብዙ ቦታዎች ላይ አደጋዎች እየደረሱ ይገኛል።

3. ወያኔ ኤርትራን ከማስገንጠሉ በተጨማሪ ጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ አካል የነበረችውን የአሰብ ወደብ በመመረቂያነት በመስጠቱ ኢትዮጵያን ለከፋ የኢኮኖሚ ችግር ዳርጓታል። ዘረኞቹ መሪዎቻችን የባህር በር የነበራትን አገራችንን ወደብ አልባ እንድትሆን ስለፈረዱባት ዛሬ ለጂቡቲ ወደብ በየዕለቱ የምታወጣው የውጭ ምንዛሬ ለህዝብ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ እጅግ በርካታ ተቋማትን ለመገንባት በዋለ ነበር። ለሃገራችን ድሃ መሆን ከሚጠቀሱ ዋነኛ ምክንያቶች ውስጥ የወደባችን ተላልፎ ለሌላ መሰጠት አንዱ እንደሆነ ምሁራን ይናገራሉ።

4. በፖለቲካ ነፃነት ማጣትና በኢኮኖሚ ችግር ምክንያት ከሃገር የሚሰደደው ወገን እየበረከተ መጥቷል። አንዳንዶቹ ስደተኞች ካሰቡበት ቦታ ሳይደርሱ በመንገድ ላይ በበረሃና በባህር ውስጥ ህይወታቸው ያልፋል። በርካታ እህቶች በአረብ ሃገራት ሰቆቃ ለተሞላበት የቤት ሠራተኝነት ህይወት ተዳርገዋል። በሌሎች አህጉራት ያሉ ወንድሞቻችንና እህቶቻችንም ሁለተኛ ዜጋ ሆነው በሰቆቃ በመኖር ላይ ይገኛሉ። በልበ ሙሉነት፣ በአትንኩኝ ባይነት እና በኩራት የሚታወቀው ኢትዮጵያዊ ዛሬ የወያኔ ሥርዓት ባመጣበት አስከፊ ህይወት ለስደት ተዳርጎ በውርደት የመኖር ዕጣ ገጥሞታል።

5. የገዥው ፓርቲ በሚያራምደው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ህዝብ በኑሮ ውድነት እጅግ እየተሰቃየ ይገኛል። የምግብ ምርቶች ዋጋ ማሻቀብ፣ የማገዶና የነዳጅ ዋጋ መናር፣ የትራንስፖርት አቅርቦት ዝቅተኛ ከመሆኑም በተጨማሪ ዋጋው ከዕለት ዕለት እየጨመረ መምጣት፣ የመኖሪያ ቤት እጥረት መኖር፣ የትምህርት ቤት፣ የሃኪም ቤት፣ የመብራት፣ የስልክና የሌሎችም አገልግሎቶች ክፍያ ከፍተኛ መሆን እና የመሳሰሉት ሁሉ ህይወት በኢትዮጵያ ውስጥ መራራ እንዲሆን አድርገውታል። ባጠቃላይ የምግብ፣ የአልባሳትና የመጠለያ እጦትና ውድነት የህዝብን ምሬት ከፍተኛ ደረጃ ላይ አድርሰውታል። እራሳቸውን ችለው ይኖሩ የነበሩ በርካታ አባ ወራ እና እማ ወራዎች ዛሬ ወደ አደባባይ በመውጣት ለልመና ተሰማርተዋል።

ሥራ አጥነት ሌላው የህብረተሰቡ ችግር ነው። ከዩንቨርስቲና ከኮሌጆች ትምህርታቸውን የሚያጠናቅቁ ምሩቃን ሥራ ስለማያገኙ በቤተሰቦቻቸው ሥር የወጣት ተጧሪዎች ለመሆን ተገደዋል። ከህንፃ ኮንስትራክሽን፣ ከቴሌ ኮሙኒኬሽን፣ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክና ከሌሎችም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ብቁ ሠራተኞች መባረራቸው ዜጎች ለረሃብ እንዲዳረጉ ማድረጊያው ሌላው የገዥው ፓርቲ እርምጃ ነው።

6. በዩንቨርስቲዎች፣ በኮሌጆችና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተማሪዎችና መምህራን የአካዳሚክ ነፃነታቸውን በወያኔ አፈና የተከለከሉ በመሆናቸው የተማሪዎች መማክርት

ሊያቋቁሙ አልቻሉም። በተለያዩ ጊዜያት የሚነሱ የተማሪዎች የመብት ጥያቄዎች በግድያ፣ በእስራትና ከትምህርት ገበታቸው ላይ በማባረር የተወሰዱት እርምጃዎች የተማሪዎች አሳዛኝ ዕጣዎች ናቸው።

7. መምህራን ለአቀረቧቸው ጥያቄዎች ምላሽ ባለማግኘታቸው ህገ መንግሥታዊ መብታቸውን ተጠቅመው የሥራ መቆም አድማ በማድረጋቸው የተወሰኑት ከሥራ ተባረዋል። ሌሎቹ ደግሞ ማስፈራሪያ ተሰጥቷቸው በግዳጅ ሥራ እንዲጀምሩ ተደርገዋል።

8. የነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ከወያኔ ኢህአዴግ ካድሬዎችና የደህንነት ሠራተኞች ማስፈራሪያና ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸዋል። ይታሠራሉ። በፍርድ ቤት ይከሰሳሉ። በገንዘብ ይቀጣሉ። በሽብርተኝነት ይወነጀላሉ። በተዘዋዋሪ ቅድመ ምርመራ ይካሄድባቸውል። ተቋሞቻቸውን እንዲዘጉ ይደረጋሉ። ከሃገር ይሰደዳሉ። ከዚህም በተጨማሪ ከውጭ ወደ ኢትዮጵያ የሚተላለፉ የአሜሪካና የጀርመን ድምፅ ሬድዮ ጣቢያዎች እንኳን የኢትዮጵያ ህዝብ እንዳያደምጣቸው ከፍተኛ ገንዘብ ወጭ ተደርጎባቸው በሞገድ ይታፈናሉ። በፖለቲካ ላይ የሚንቀሳቀሱ ድረ ገጾችም እንዲሁ ይዘጋሉ። ይህም ህዝቡ ወቅታዊ ሁኔታዎችን እንዳይከታከልና በሃገሩ ጉዳይ ላይ የመፍትሔ ሃሳብ እንዳይሠጥ የማድረግ ተግባር ነው። በአሁን ወቅት በስፋት የሚለቀቁት እጅግ አሰልቺና አደንቋሪ የሆኑት የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥ ፕሮፖጋንዳዎች ናቸው።

9. በየጊዜው የሚካሄዱ አገር አቀፍና የክልል ምርጫዎች በአምባ ገነኑ ወያኔ ኢህአዴግ መንግሥት ይጭበረበራሉ። ተወዳዳሪዎች፣ ታዛቢዎችና መራጮች የተለያዩ ተጽዕኖዎች ይደረሱባቸዋል። ለምሳሌ በ1997 ዓ.ም በተካሄደው ብሔራዊ ምርጫ የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ምርጫውን ማሸነፍ ተከትሎ ወያኔ ስልጣኑን ላለመልቀቅ ሲል የተለያዩ አሰቃቂ እርምጃዎችን ወስዷል። ድምፃችን ይከበር ብሎ በወጣው ሰለማዊ ሰልፈኛ ላይ የተኩስ እሩምታ ከፍቶ የብዙዎችን ህይወት ቀጥፏል። በሃሪቱ የተለያዩ ክፍሎች የማጎሪያ እስር ቤቶችን በማዘጋጀት እጅግ በርካታ አመራርና አባላትን እንዲሁም ደጋፊዎችን አንገላትቷል። ብዙዎችንም አሰድዷል። እርምጃዎቹ የሥርዓቱን አስከፊነት በግልጽ አሳይተዋል።

የ2002 ዓ.ም ምርጫ አካሄዱና ተገኘ የተባለው 99.6% ውጤት የወያኔን ፍፁም አባገነንነትና መድበለ ፓርቲ ሥርዓት በኢትዮጵያ ውስጥ የተሚጠጠ መሆኑን በገሃድ አሳይቷል።

10. በአማሪኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ጉራ ፋርዳና መተከል ላይ፣ በአኙዋክ፣ በአፋሮች እና በሌሎችም ብሔረሰቦች ላይ ከሚኖሩበተ ቀዬዎች የማፈናቀል እርምጃዎች ተወስደውባቸዋል። በዚህም ነፍስ ጡሮች፣ እመጫቶችና ህፃናቶችን ጨምሮ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች በመንግሥት ታጣቂዎች የኃይል እርምጃ እየተወሰደባቸው በተለያዩ ቦታዎችና በርሃ አካባቢዎች እንዲበተኑ መደረጋቸው ወያኔ ታላቅ ሃገራዊ ውርደትን በኢትዮጵያውያን ላይ እየፈፀመ መሆኑን ያሳያል። በሌሎችም አካባቢዎች በቀጥታና በተዘዋዋሪ በአርሲ፣ በባሌ፣ በወለጋና በሌሎችም የደረሰው ግድያና የህዝብ መፈናቀል የሥርዓቱን አስከፊነት መጨረሻ ደረጃ ላይ መድረሱን ይገልፃል።

11. የሰብአዊና የዲሞክራሲያዊ መብቶች በመታፈናቸው ህዝባችን ማንኛውንም ተፈጥሮአዊ የሰው ስሜቶችን ለመግለጽ አቅቶታል። በመሆኑም ህዝቡ እየደረሱበት ያሉትን ረሃብ፣ የመኖሪያ ቤት እጦት፣ ሌሎችም ችግሮችን ለመግለጽ አልቻለም። ሰላማዊ ሰልፍና ህዝባዊ ስብሰባ ማካሄድ፣ የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ እና በፖለቲካ መደራጀት የህይወት ዋጋ የሚያስከፈሉ ሆነዋል።

12. ህገ መንግሥታዊ መብታቸውን ተጠቅመው የተቋቋሙ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አመራሮችና አባላት በየጊዜው ግድያ ይፈጸምባቸዋል። በተለይም በመኢአድ ላይ ከፓርቲው መሪ ከፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ አንስቶ እስከ ዞን፣ ወረዳ እና ቀበሌ አመራሮች ድረስ ያሉ መሪዎችና አባላት ተገድለዋል። ብዙዎች ታስረዋል። ከመንግሥት ሥራ ተባረዋል፤ ከደረጃ ዝቅ ተደረገዋል። ከመሬታቸው ተነስተዋል። ቤቶቻቸው እንዲቃጠሉ ተደርገዋል። ከቀያቸው አንዳንዶቹም ከሃገራቸው

Central Executive Office
...HIOPIA UNITY PARTY AEUP

ተሰደዋል። የወያኔ ኢህአዴግ ካድሬዎች እነዚህና ሌሎችም ሰቆቃዎች መፈጸም የዘወትር ተግባራቸው አድርገውታል።

13. በህዝቡም ላይ በአዲስ አበባ፣ በአዋሳ፣ በባህር ዳር እና በሌሎችም አካባቢዎች በፌደራል ፖሊስ፣ በአጋዚ ጦርና በሌሎችም ታጣቂ ኃይሎች የተፈጸሙት የግድያ እና የማቁሰል እርምጃዎች የሰዎችን ሰላማዊ ጥያቄ ለማፈን የተደረጉ መሆኑ አይካድም።

14. የገዥው ፓርቲ በሚከተለው የመሬት ፖሊስ መሬት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያለ በመሆኑ አርሶ አደሩ የመሬቱ ባለቤት እኔ ነኝ ብሎ ሊያድግበት አልቻለም። የገዥው ፓርቲ መሬትን የፖለቲካ መሳሪያ በማድረጉ በፈለጉት ጊዜ ከእጁ በመንጠቅ ለእንግልት ሲዳርጉት ይታያሉ። ገበሬው ከፈቃዱ ውጭ ማዳበሪያ በግዴታ እንዲገዛ መደረጉ ሌላው የአርሶ አደሩ ፈተና ነው። በተጨማሪም የከተማ ነዋሪም የቤት መሥሪያ መሬት ባለቤትነቱን ተገፏል።

15. አድሎአዊ የንግድ ሥርዓት በመስፋፋቱ የሃገር ሃብት በጥቂት ለሥርዓቱ ታማኝ በሆኑ ግለሰቦች እና ቡድኖች እጅ እንዲገባ እየተደረገ ነው።

16. የመንግሥት ሠራተኞች፣ ተማሪዎች፣ ገበሬዎች እና ሌሎችም የህብረ ተሰብ ክፍሎች ከፍላጎታቸው ውጭ የኢህአዴግ ፓርቲ አባል እንዲሆኑ መገደዳቸው ህዝብ በገዛ አገሩ ኑሮ በበለጠ መሮት ለፍልሰት ተዳርጓል።

17. የምርጫ ቦርድ የገዥው ፓርቲ አገልጋይ መሆን፣ የፍትህ አካላት ብዙ ጊዜ ገለልተኛ የሆነ ፍርድ አለመስጠት፣ ለወገንና ለሃገር ጥበቃ ማገልገል የሚገባቸው የፖሊስና የደህንነት ኃይሎች የገዥው ፓርቲ መሳሪያዎች መሆናቸው፣ የመንግሥ ሜዲያዎች ለአገዛዙ የልሳን ያህል ማገልገላቸው እና የመሳሰሉት የህዝባችንን ሥቃይ በማባባስ የሃገራችንን ህልውና አደጋ ላይ ጥለውታል።

ወያኔ ኢህአዴግ በ21 ዓመት አገዛዙ ኢትዮጵያ አገራችንን ህዝብ የሚቆላባትና የሚንገረገብባት የምድር ሲኦል ሆናለች። ዛሬ በሃገራችን የህዝብ ብሶት ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ መጥቷል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ለመብቱ ታግሏል። አሁንም በመታገል ላይ ይገኛል። ነገር ግን ለተደጋጋሚ ጊዜያት የትግል ፍሬው በሌሎች ተቀምቶበታል።

አንደኛው፦ የአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ሲያበቃ ሥልጣን በወታደራዊ ጁንታ መያዙ፣

ሁለተኛው፦ የወታደራዊው ሥርዓት ሲያከትም ጠመንጃ ጨብጦ የጎሳ ፖለቲካ በሚያራምደው ህወሃት እጅ ሥልጣን መግባቱ፣

ሦስተኛው፦ ህዝብ በምርጫ 97 ከዳር እዳር ተነቃንቆ የወደደውን ቢመርጥም አምባገነኑ ወያኔ ውጤቱን በጠመንጃ ቀምቶ በሥልጣኑ ላይ መቆናጠጡ ናቸው።

የህዝብ ብሶት ከፍተኛ ደረጃ ላይ በመድረሱ በትግሉ ለዘመናት የተነፈገውን ሥልጣን የሚረከብበት ጊዜው ተቃርቧል። እስከዛሬ ብዙ ደም ፈሰሰ፤ በርካታ የአካል ጉዳቶች ደረሱ፤ የህዝብና የግለሰቦች ንብረትም ወደመ፤ የአገር ኢኮኖሚም ተናጋ። ከዚህ በኋላ ግን እንደመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) እምነት በሰለጠነው አካሄድ ሥልጣን ያለ ደም መፋሰስና እልቂት ወደ ህዝብ ሊተላለፍ ይገባል እንላለን።

## ለብሔራዊ የኮንፍረንስ ጥሪ መነሻ ሃሳቦች እና አስፈላጊነቱ

ህዝብ በሃገሩ ጉዳይ ሊመክር እና የሚበጀውን ሊወስን ይገባል። ዛሬ ሃገራችን በሚያሳስብን ሁኔታ ላይ ትገኛለች። በረጋና በሰከነ መንፈስ በመወያየት መፍትሔ መሻት ያስፈልጋል። ኢትዮጵያ የሁሉም ኢትዮጵያውያን ናት። የባለሥልጣኖችም የሥልጣን አልባዎችም፣ የሃብታሙም የደሃውም፣ የከተሜውም የገጠሬውም፣ የስደተኛውም በሃገረ ውስጥ ኗሪውም፣... የሁሉም እናት ናት። ታዲያ የሁላችንም እናት በሆነችው የኢትዮጵያችን ጉዳይ ሁላችንም የመምከር እና የመወሰን መብት አለን።

በጠመንጃ አፈ ሙዝ አሸንፈው ሥልጣኑን ለሃያ አንድ ዓመት የያዙት አምባ ገነኖች ይህን ወንበር በሰላማዊ መንገድ ለህዝብ ሊያስረክቡ ግድ የሆነበት ጊዜ ላይ ደርሰናል።

በወያኔ ኢህአዴግ አገዛዝ ህዝብ እጅግ የተመረረበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ዛሬ ከብሶት ብዛት የተነሳ ሰዎች ራሳቸውን በቤንዚን አርከፍክፈው በእሳት ነደው እመሞት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። በደቡብ ኢትዮጵያ ዳውሮና በአዲስ አበባ አራዳ ጊዮርጊስ አካባቢ እራሳቸውን ያቃጠሉትን ሁለት ሰዎች ልብ ይሏል። ስለዚህ የወያኔ አመራሮች በአሁን ወቅት ብልህና አስተዋዮች ሆነው በብሔራዊ ኮንፍረንሱ በመሳተፍ ለህዝባችን ሰላማዊ ህይወትን የሚሰጠወን መፍትሔ በጋራ ሊፈልጉ ይገባል።

አሁን ያለንበት ፖለቲካዊ ቀውስ፣ የዜጎች የጅምላ እስር፣ አገራችንን በዓለም ህዝብ ፊት በአዋረደ መልኩ እየተካሄዱ ያሉ ስደቶች፣ በህዝብ ላይ እየደረሰ ያለ ችጋር፣ በየክልል ድንበሮች እየተፈፀሙ ያሉ ደም አፋሳሽ ግጭቶች፣ ሥራ አጥነት፣ የከፋ ሙስና፣ ሰብአዊ ረገጣ ፣እየተባበሰ የመጣው ህዝባዊ ብሶት እና ሌሎችም የህዝብ ሃዘንና ሰቆቃ ለዚህ ሰነድ መዘጋጀትና ሁሉን አቀፍ ኮንፍረንስ እንዲካሄድ ጥሪ ለማድረግ ግፊት አድርገዋል።

በቅድሚያ በመላው ሃገሪቱ የታሠሩ የፖለቲካ እስረኞች፣ ጋዜጠኞች፣ የሃይማኖት ሰዎች፣ ተማሪዎችና ሌሎችም መንግሥትን በፖለቲካ ከመቃወም ሂደት ጋር በተያያዘ የታሠሩ በሙሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ እና የኮንፍረንሱ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ።

በአሁን ወቅት ጥቂት የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችን ብቻ በማካተት ከኢትዮጵያ ውጭ በጉሳ እና በልዩ ጥቅም በአሜሪካና በአውሮፓ በተናጠል እየተካሄዱ ያሉት ስብሰባዎች ለህዝብ ጥያቄ የሚፈለገውን ምላሽ ይሰጣሉ የሚል እምነት የለንም። የተለያዩ የአስተሳሰብ ልዩነቶች ቢኖሩንም እንኳን ቅድሚያ የሚሰጠው አገርና ህዝብን ማዳን ስለሆነ አሁን በተናጠል የምታካሂዱትን ስብሰባ አቋርጣችሁ የሁሉም ፓርቲዎችና ሌሎች አስፈላጊ አካላት የሚያካሂዱት መፍትሔ አምጭ ኮንፍራንስ እንዲካሄድ እንቅስቃሴ እንድታደርጉ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ጥሪ ያቀርባል።

በሃገራችን ያለውን አጠቃላይ ቀውስ በሰላማዊ መንገድ ወደተስተካከለ ሁኔታ ለመቀየር የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት የሚከተሉትን የመፍትሔ ሃሳቦች ያቀርባል። ሙሉ ሰነዱንም በቅርብ ይፋ ያደርጋል።

**በአገር ውስጥ እና ከአገር ውጭ የሚገኙ በሰላማዊም ሆነ በትጥቅ ትግል ውስጥ ያሉ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የተቋቋሙ ፓርቲዎች በሙሉ እንዲሁም ሲቪክ ማህበራት፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ ምሁሮች፣ አርሶ አደሮች፣ ነጋዴዎች፣ ሠራተኞች፣ የገዥው ፓርቲ ተወካዮች እና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በሃገራዊ ኮንፍረንስ ላይ ተገኝተው በመመካከር ሃገራችን ወደ ሁከትና የእርስ በርስ ብጥብጥ ሳትገባ ህዝብ በሰላማዊ መንገድ የሥልጣን ባለቤት የሚሆንበት መፍትሔ ሊያበጁ ይገባል።**

ይህ ጉባዔ ህዝብን ከእልቂት ኢትዮጵያንም ከውድቀት ለማዳን በሚችሉ የመፍትሔ አቅጣጫዎች ላይ በጥልቀት የሚወያይ ይሆናል።

## <u>ከብሔራዊ ኮንፍረንሱ የሚጠበቁ የመፍትሔ አቅጣጫዎች</u>

1. የኮንፍረንሱ ተሳታፊዎች ያለፉ ጊዜያት ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን ገምግመው ችግሮችን በጋራ ነቅሰው በማውጣት አዲስ ፖለቲካዊ አቅጣጫዎችን ይቀይሳሉ።

2. በአገራችን የደረሱት አሰቃቂ የህዝብ ስቃዮች የደረሱት በወያኔ ኢህአዴግ መንግሥት በመሆኑ የኃላፊነቱ ሥፍራ በኮንፍረንስ ተሳታፊዎቹ በሚመረጡ ጊዜያዊ የሽግግር ካውንስል መተካት የግድ ይሆናል። ይህ ዋናውና እጅግ አስፈላጊዊ ጉዳይ ነው።

3. የተለያዩ አስተዳደራዊና ዲሞክራሲያዊ ተቋማት በፖለቲካ ፓርቲዎች ኮንፍረንስ ውሳኔ መሠረት በሚቋቋም ገለልተኛ ቡድን አማካኝት በፍጥነት በአዲስ መልክ እንዲደራጁ ያስፈልጋል። በገለልተኝነት እንዲደራጁ ከሚፈለጉ ተቋማት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የፍትህ ተቋማት፣ የሚዲያና የማስታወቂያ ተቋማት፣ የብሔራዊ ምርጫ አስተባባሪ፣ የደህንነት ተቋም፣ እና ሌሎችም ይሆናሉ።

4. አሁን ያለው ህገ መንግሥት አንዳንድ አንቀጾች ለምሳሌ፦ የአገራችንን አንድነት የሚያናጉ፣ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሂደትን የሚያግዱ፣ ተቋማዊ ጥንካሬና ግንባታን የሚያበረታቱ፣ አገራዊ ልማትን፣ እድገትን፣ ሰላምና ፍቅርን የሚያስተጓጉሉ እና የአፈጻጸም ችግር ያለባቸው አንቀጾች በአስቸኳይ እንዲሻሻሉ፤

5. የሙስሊሞች ጥያቄ ምላሽ እንዲያገኝ፤

6. የዋልድባ ገዳም ይዞታ ቀድሞ በነበረበት ሁኔታ እንዲመለስ፤

7. ከጉራ ፋርዳ፣ ከአፋር፣ ከመተከል እና ከሌሎችም አካባቢዎች የተፈናቀሉ ኗሪዎች ወደ ነበሩበት ሥፍራ እንዲመለሱ፣

8. በነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ላይ እየተካሄደ ያለው አፈና እንዲቆም፣ የተዘጉ የሚዲያ ተቋሞቻቸው እንዲከፈቱ፣ የተጣለባቸው የገንዘብ ቅጣት እንዲነሳ፤

9. የመምህሩ ጥያቄ ምላሽ እንዲሰጣቸው፤ ከሥራቸው የተባረሩ መምህራን ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ፤

10. ከቴሌ ኮሙኒኬሽንና ከሌሎችም መስሪያ ቤቶች የተባረሩ ሠራተኞች ወደ ሥራቸው ይመለሱ፤

11. የአቶ መለስ ዜናዊ ህመም እና የማረፋቸው ዜና በሹክሹክታ መሰማት ከጀመረ አንስቶ የኢህአዴግ ባለሥልጣናት ብቻቸውን በምሥጢር የሚያካሂዱት ዱለታና ሽኩቻ እንዲሁም የተለያዩ እንቅስቃሴዎች በሃራችን ላይ የሚያስከትሉት ቀውሶች እጅግ ከባድ በመሆናቸው ባስቸኳይ ሊያቆሙ ይገባል። ይኸውም ባለሥልጣናቱ የስውር እንቅስቃሴያቸውን አቋርጠው ለኢትዮጵያ የጋራ መፍትሔ ሊያመጣ ከሚችለው ከብሔራዊ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ሌሎች አካላት ከሚገኙበት ኮንፍረንስ ጋር በጋራ ለመሥራት መወሰንና ለኮፍረንሱ መካሄድም ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል። ይህ ውሳኔ ደግሞ ለሃገርም ሆነ ለራሳቸው ለውሳኔ አስተላላፊዎቹ የሚበጅ ይሆናል።

የኢትዮጵያውያን ብሶት ገንፍሎ ህዝብ አደባባይ ከወጣ የወያኔ ባለሥልጣናትና ካድሬዎቻቸው በሊቢያ እንደሆነው የእነ ኮለኔል ጋዳፊን ዓይነት ጽዋ ሊጎነጩ እንማችሉ መገንዘብ ይኖርባቸዋል። ሥልጣንን ለህዝብ በማስረከብ ጉዳይ ላይ የወያኔ ኢህአዴግ ባለሥልጣናት ቁርጠኛ ውሳኔ ማድረግ ያስፈልጋቸዋል። ይህ በእጃቸው ያለ ወርቃማ ዕድል ነው። ዕድሉን ፈጥነው ሊጠቀሙበት የግድ ይላል። የሊቢያ፣ የግብጽ፣ እና የቱኒዚያ አንባ ገነን መንግሥታት ዛሬ በሥልጣናቸው ላይ የሉም፤ ህዝባዊ አመጽ ጠራርጎ የሙጢኝ ካሏቸው ወንበሮቻቸው ላይ አውርዷቸዋል። የእኛዎቹ ገዥዎች ከእነሱ ትምህርት ወስደው ባስቸኳይ ወደ ሰላማዊ መፍትሔ ሊመጡ ይገባል።

## ለብሔራዊ ኮንፍረንሱ መሳካት የተላለፉ ጥሪዎች

ከላይ የዘረዘርናቸው አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች ዋናው ባለቤት የኢትዮጵያ ህዝብ ነው። የሃገራችን ገዥ መደቦች ለዘመናት የራሳቸውን ፍላጎት ለማስፈጸም ሲሉ

የህዝባችንን ህይወት ወደ ከፋ ሁኔታ ሲጨምሩት ቆይተዋል፤ አሁንም እንደዚሁ፡፡ የገዥዎች ፍላጎት ዛሬ በፍጥነት አብቅቶ በኢትዮጵያ ህዝብ የሥልጣን ባለቤትነት መተካት አለበት፡፡

ከላይ የገለጽናቸውን የብሔራዊ መግባቢያ ነጥቦችን በማስፈጸም ሂደት ውስጥ ዓለማቀፉን ማኅበረሰብ ማሳተፍ ይገባል፡፡

ዛሬ ኢትዮጵያ ለዲሞክራሲ፣ ለሰላም፣ ለፍትህ እና ለብልጽግና የቆመ ሥርዓት ለመመሥረት ወይም በተቃራኒው አሁን ካለንበት በባሰ አስከፊ አንባገነን ደም አፋሳሽ ሥርዓት ሥር መውደቅ በመንታ መንገድ ላይ ትገኛለች፡፡ ስለዚህ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ማንኛውም ለኢትዮጵያ ሰላምና አንድነት የቆመ የፖለቲካ ቡድን፣ የሲቪክ ማኅበረሰብ፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ የሠራተኞች ማኅበር፣ የመምህራን፣ የጋዜጠኞች፣ የወጣት እና ሌሎችም ማኅበራት በሙሉ ለሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት እና ይህን ተከትሎ ለምትመሠረተው አዲሲቱ፣ ጠንካራና ሰላማዊ ኢትዮጵያችን ዘብ እንድትቆሙ ጥሪ ያስተላልፋል፡፡

**የተወደዳችሁና የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!** የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት የሚሆንበት ሁሉን አቀፍ ኮንፍረንስ እንዲካሄድ ያቀረበው ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ግቡን እንዲመታ እናንተ የትግሉ ባለቤት መሆናችሁን ተገንዝባችሁ ከጎናችን ትቆሙ ዘንድ ጥሪ እናስተላልፋለን፡፡ ለብሔራዊ፣ የሰላምና የአንድነት መንግሥት ምሥረታ ሰነድ አፈጻጸም ስኬትም እንደዚሁ ከጎናችን እንደምትቆሙ ተስፋችን ብርቱ ነው፡፡

**ውድ ምሁራን!** ኢትዮጵያ ጥሪቷን አፍስሳ ያስተማረቻችሁ ምሁራን ወገኖቻችን በዚች ወሳኝ ቀን ለኢትዮጵያ ችግሮች መፍትሄ ለመሻት የመፍትሄው አካል ሆናችሁ ወደ ትግሉ እንደትገቡ መኢአድ ጥሪ ያስተላልፋል፡፡

**የተከበራችሁ የደህንነትና የመከላከያ ሠራዊት!**

የፖሊስ እና የወታደር ተቋማት የተመሠረቱት የሃገርንና የህዝብን ጸጥታና ደህንነት ለመጠበቅ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለዚህ ይህንን ቃል ገብታችሁ የተሰማራችሁበትን ዓላማ ጠብቃችሁ በዚህ እጅግ ወሳኝ ወቅትም የወገን አለኝታነታችሁን፣ የህዝብ ተቆርቋሪነታችሁን እና ፈጥኖ ደራሽነታችሁን እንድታሳዩ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት አደራ ይላችኋል፡፡

**በውጭ ሃገር የምትገኙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን!** በኢትዮጵያ መልካም አስተዳደር ለማስፈን በተለያዩ መንገዶች ትግል ስታደርጉ መቆየታችሁ ይታወቃል፡፡ አሁንም ህዝብ የሥልጣን ባለቤት የሚሆንበት ሁሉን አቀፍ ኮንፍራንስ እንዲካሄድ ጥሪት በማድረጉ እረገድና በሌሎችም አስፈላጊ ጉዳዮች ሁሉ ከጎናችን እንድትቆም ጥሪ እናቀርባለን፡፡

**ኢትዮጵያ በሰላማዊ መንገድ ወደ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ትሸጋገራለች!!!**

**ነሃሴ 15/2004**
**አዲስ አበባ**
**ኢትዮጵያ**